የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 85 ቁጥር 2(986)

“ሁሉም በእርሱ (በክርስቶስ) ተጋጥሞአል” (ቆላስያስ 1፥18)

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያና የመጨረሻ አልፋና ዖሜጋ ነው

(በኤ.ቢ ሲምፕሰን/A.B. Simpson)

“እልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ” (የዮሐንስ ራእይ 22፥13)

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመሪያና መጨረሻው መሆኑ እጅግ አስደሳች ጉዳይ ነው።

የመጀመሪያነቱ ዖሜጋ መሆኑ እርሱ ከምንም በፊት የነበረ ፈጣሪ አምላክ መሆኑን የሚያሰረዳ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን መንገድ አዘጋጅ የተባለውም ስለ ክርስቶስ ቀዳሚነት መስክሯል፤ “እርሱ ከእኔ በፊት ነበር” (ዮሐንስ ወንጌል 1፥30)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከአባቱ እቅፍ እምቅድመዓለም እንደ ነበርና ከዚያ እንደ መጣልን የእምነት አባት ከተባለው አብርሃም በፊትም መኖሩን አስተምሯል (ዮሐንስ 8፥58፣ 16፥28)። ነቢዩ ኢሳይያስም በትንቢት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የዘላለም አባት ብሉ ትንቢቱን ጽፎልናል (ኢሳይያስ 9፥6)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ አምላክና ሰው መሆኑ በቃሉ ተጽፏል (ቆላስይስ 1፥18)። ይህን ፈጣሪነቱንና አምላክነቱን ጠብቆ በሰው አምሳል ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተጸንሶ በመወለድ የሰውን ዘር ለማዳን መጣልን (ዮሐንስ ወንጌል 1፥12፣ 1÷19)።

በብሉይ ሥርዓት የነበረው በበግ መሥዋዕት ምሳሌነት ይስሐቅ ሊሠዋ የነበረውን አብርሃም የእምነት አባት ሊፈጽም የነበረውን ተከትሎ ክርስቶስ እንደ በግ ለመታረድ ከኃጢአት ሁሉ አዳነን (ዘፍጥረት 22፥1፣ ራእይ 5፥12)።

በክርስቶስ መሥዋዕትነት ደኅንነት ያገኘን ሁላችን ይህን ታላቅ መዳን ለሌሎች እንድንመስክር የመዳናችን ምክንያትና ዋና ፈጻሚ አልፋና ዖሜጋ የመጀመሪያና መጨረሻ የሆነውን ክርስቶስ በሚገባ በማወቅ ልንከተለው ይገባል።

ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሳይወለድ በፊት አምላክ የነበረ በምድረ በዳ ለተጠሙ እስራኤላውያን የዓለት ውኃ ምንጭ የሆነና ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎን በእሳቱ መካከል ተገኝቶ ያዳነ ዘላለማዊ አምላክ ነው (ዘጸአት 17፤ ኢሳይያስ 48፥2፤ ዳንኤል 3፥25)። ክርስቶስ በክብር ይመለሳል፤ ተዘጋጅተን እንጠብቀው :: (ሐዋርያት 1፥11)።

በክርስቶስ እርስ በርስ እንበረታታ፤ እንተናነጽ

(በሪች ካርማይክል/Rich Carmichael)

በየምጽአቱ የምሥራች አገልግሎት የተሰማራን ሁላችንም እርስ በርሳችን ስላለን መተናነጽና መበረታታት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን።

ወደ ሃያ በሚጠጉ የዓለማችን ቋንቋዎች፣ አማርኛን ጨምሮ፣ እየተተረጎመ በመላው ዓለም የሚሰራጨው ይህ የወንጌል አገልግሎት ለብዘዎች መዳን፣ መነቃቃትና መተናነጽ ምክንያት ሆኗል።

(በኢትዮጵያም ይህ የትርጉም አገልግሎት እንዲጀመር አዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደራሲ ደረስ ብሩ እየተጋበዘ ያስተምራቸው የነበሩት የሰንበት ተማሪዎች ጥያቄያቸውን ለአሜሪካ ካንሳስ አሳታሚው ባቀረቡት መሠረት፣ ትርጉሙ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል።)

ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉና በሁሉ የሆነ አልፋና ዖሜጋ የመጀመሪያና የመጨረሻ አምላክ ነው (ራእይ 22፥13)። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ወክሎና ሆኖ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ሊያድነን መጣ (ቆላስይስ 1፥15)።

ክርስቶስ ለዘለዓለም የነበረ ሁሉም በእርሱ የተፈጠረ ጌታና ፍጹም ሰውና አምላክ ነው (ዮሐንስ 1፥4)።

የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር በሙላት መረዳት የሚቻለው በቅዱስ ቃሉና በቅዱስ መንፈሱ በመሞላት ብቻ ነው (ሐዋርያት 26፥18፤ 1 ዮሐንስ 5፥11)።

እማኞች እርስ በርሳችን በቅዱስ ቃሉና በፍቅሩ ሰንበረታታና ሰንደጋገፍ የክርስቶስ ብርሃን በእኛ ውስጥ እየመጣ በዓለም ያሉትን ሁሉ ከጨለማ በማውጣት ወደ ዓለም ብርሃን ክርስቶስ ያመጣቸዋል (ዮሐንስ 13፥34፤ 1 ዮሐንስ 4፥12)።

በዚህ እትም ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት እያጠነከረ እርስ በርሳችን ላለን አስፈላጊ ኅብረት እንዲረዱ የተዘጋጁ መልእክቶች ይገኙበታል።

በተሰፋ የምንጠብቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ቃሉ እስኪመለስ ድረስ በዚህ ቃሉና በተሰፋው እርስ በርስ እንበረታታ (ወደ ዕብራውያን 10፥25)።

የክርስቶስ ዘላለማዊ ፍቅር በመሰቀሉ ተገለጸ

(በኦክታቨስ ዊንስሎው/Octavius Winslou)

“እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ” (*1 ጴጥሮስ 2፥24)።*

የእግዚአብሔር እጅግ ልዩ የሆነው ለሰው ዘር ሁሉ ያደረገው የፍቅር ሰጦታ አንድያ ልጁ፣ ሰውና አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ዘርን ከጥፋት ለማዳን በመሰቀል መከራ ሕይወቱን መሰጠቱ ነው። በዚህ የመሰቀል ሥራ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር ለሰዎች ሁሉ ተገልጧል።

ወደ መሰቀሉ ልንሄድ ወይም ምልክቱን በሰዎችና በሕንፃዎች ላይ ሰንመለከት ልናሰበው የሚገባው ትልቁ ጉዳይ በዚያ መሰቀል ላይ ሁላችንም በነበረው የሮማ ሕግ መሠረት ልንሰቀልና ልንቀጣበት የነበረውን በደላችንን ሁሉ ክርስቶስ ተቀብሎ በእኛ ፈንታ መሞቱን ነው።

እንዳንዶቻችን ኃጢአትና በደላችንን በማሳነስ ከሌሎች የተሻልን መሰሎ ቢታየንም፣ ቅዱስ ቃሉ ሁላችንም እንደ በደልንና ፍርድ እንደሚገባን ይነግረናል (ወደ ሮሜ መልእክት 3፥23)።

ሌሎቻችን ደግሞ የሠራነውና የምናደርገው መሥዋዕትና ተሳትፎ ለበጎ ሽልማት እንደሚያበቃንና ፍርድ እንደማይገባን ብንመካም፣ ቅዱስ ቃሉ ጽድቃችንና በጎ የምንለው ሥራችን ሁሉ የመርገም ጨርቅና የነውር መሸፈኛ ብቻ እንደ ሆነ እያሳብን በሥራችን ሳይሆን፣ በጌታ ሥራ እንድንታመን ያደርገናል (ትንቢተ ኢሳይያስ 64፥6፤ ኤፌሶን 2፥8)።

ሆኖም ግን፣ ክርስቶስ በመገረፉ፣ በመዋረዱና በመሰቀል ሞቱ የእኛ የሰው ልጆች በደል ሁሉ እንደ ተሻረልንና በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ቅዱሳን እንድንሆን የወንጌል ፍቅሩ ይጠራናልና እንቀበለው፤ ሌሎችም እንዲቀበሉት እንመስክር (ሮሜ 1፥7፣ 8፥29፤ 1 ቆሮንቶስ 1፥2፤ ኤፌሶን 1፥1)።

ክርስቶስ ይቅደም በኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ

(የአማርኛው ትርጉም አስተባባሪ)

በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በገናናዋ አሜሪካ ሀገራቸው እንድትቀድም የሚሰነዘሩ ጥቅሶች ይገኛሉ፡- “ኢትዮጵያ ትቅደም!”

“አሜሪካ ትቅደም!”

እነዚህ መፈክሮች የሚስተጋቡት ዜጎች የራሳቸውን ጥቅም ሳይሆን የሀገራቸውን ጥቅም እንዲያስቀድሙ በመመኘት ስለ ሆነ፣ መልካም ሐሳቦችና ምኞቶች ናቸው።

ሆኖም ግን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን በትክክል እንዳስተማረው፣ ሊቀድም የሚገባውን ነገር ሳናስቀድም ተከታዩን ማስቀደም ወይም መጠየቅ የተገባ እንዳልሆነ ነው፡- “ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨምርላችኋል” (ማቴዎስ 6፥33)።

ዘላለማዊ የሆነውን የምድርና የሰማይ በረከት ሁሉ ምንጭ የሆነውን የእግዚአብሔርን የፍትሕና የፍቅር መንግሥትና ሕይወት ሳንፈልግ ሌላውን ብንፈልግ፣ ምንኛ ጎስቋላ እንሆናለን? እንመለስና የበለጠውን እንፈልግ።

የሀገራችን ችግሮች እንዲወገዱ፣ እኩልነትና ፍትሕ እንዲሰፍን መፈለጋችን የተገባ ጉዳይ ቢሆንም፣ መጀመሪያ ከልባችንና ከውስጣችን የፍቅር፣ የፍትሕ፣ የእኩልነትና የሰላም ምንጭ የሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት እውነተኛ መሻትና ሕልውና ከሌለን፣ በውጭ የምንመኘው በጎ ነገር ሁሉ የታይታ ይሆናል።

እግዚአብሔርን በእውነተኛ ልብ በንስሐ ብንጠይቀው፣ እርሱ ራሱ የበጎ ነገሮች ሁሉ ምንጭና ፈጣሪ አምላክ ከቸርነቱና ከምሕረቱ ብዛት የተነሣ በጎ ሰጦታዎቹን ሁሉ ያፈሰልናል። “በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ስውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ” *(2 ዜና* መዋዕል *7፥14)።*

“በሰውር ያለው አባትህ በግልጥ ይከፍልሃል” *(*ማቴዎስ *7፥7)*

ክርስቶስን ያማከለ ሕይወት

በኤ ሬንሽሚት (Reinschmit)

ክርስቶስን ያማከለ ሕይወት ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ ያመነ ሕይወት ነው። እንድ ሰው ክርስቶስን ያማከለ ሕይወት የሚኖረው በክርስቶስ ለመታመን በራሱ ከመታመን ሲወጣ ነው።

በራስ መተማመን የተገባ ጉዳይ ነው። ራስን መጣልና ከሌሎች ሁሉ የበታች ማድረግ የማይገባ ሲሆን፣ ከዚህ በተቃራኒ እኔነት የነገሠበትና ክርስቶስን ያልታመነ የክርስትና ሕይወት ክርስትና የሌለበት ነው። “በእንተ ላይ ታምናለችና በእንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ” (ኢሳይያስ 26፥3)።

የእንድ ሰው ሕይወት በሙላት በክርስቶስ ላይ ሲደገፍ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና በረከቱ ከራሱ አልፎ ለሌሎችም የተረፈ ይሆናል።

ያለ መታመንና ያለ መታዘዝ በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነትን ይጎዳል፣ ያሰወግዳል። “ወዳጆች ሆይ፥ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን” (1 ዮሐንስ 3፥21)። “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው” (ገላትያ 2፥20)።

“መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥ በእርሱም ታመን፥ እርሱም ያደርግልሃል” (መዝሙረ ዳዊት 36፥5)።

በጌታ መታመን ከከፍታ ወደ ከፍታ ያሸጋግረናል፤ በእርሱ ብንታመን፣ ከወደቅንበት ያነሣናል።

ሰዎች በክርስትና ሕይወት የሚያዝኑበትና በጥያቄ የሚሞሉት መታመን ከሚገባቸው ከክርስቶስ ላይ እምነታቸውን ባነሡ ጊዜ ነው። ጌታ እንደ ገባልን የተሰፋ ቃል የሚሰጠን ትእዛዝ ቀላል የሆነና ልንሸከመው የምንችለውን ብቻ ሰለ ሆነ፣ ታምነነው እንታዘዘው (ማቴዎስ 11፥28)።

አሮጌ ሰዋችን (እኛነታችን) ሁልጊዜ በሕይወታችን ላይ ችግርና ፈተና ያስከትልብናል። እኛ ግን በቃሉ እየታዘዝን፣ አሮጌ ሰዋችንን (እኛነታችን) በመግፈፍ አዲሱን ክርስቶስን እየለበስን፣ በድል እምነት እንገሰግስ (ቆላስይስ 3፥9፤ 2 ቆሮንቶስ 11፥3)።

ሁሉ በሁሉ በሆነው ክርስቶስ ሁሉን ማሸነፍ እንችላለን

በቶማስ ዋትሰን (Thomas Watson)

“ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ” (ፊልጵስዮስ 4፥13)። “ክርስቶስ ሁሉ ነው በሁሉም ነው” (ቆላስይስ 3፥11)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮታዊነቱ ሁሉ በሁሉ፣ ሁሉን ቻይ ጌታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይታመን አንድ አማኝ እንዴት በእምነት ድል መነሣት ይችላል? ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕሩን፣ ሞገዱንና ነፋሱን ጸጥ ካላደረገልን፣ በሕይወታችን የሚፈራረቁ ችግሮችና ፈተናዎች ሁሉ ሊቆሙ አይችሉም።

ነገር ግን በበጉ ደም በክርስቶስ መከራ፣ መሥዋዕትነትና ድል እኛ አማኞች ከሳሽ ዲያቢሎስና ተባባሪዎቹን ድል ማድረግ እንችላለን (ራእይ 12፥11)። ይህ የድል-ነሺ ሕይወት በእኛ እንዲኖር ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር አምላክና አማላጅ ሆኖ ይጸልይልናል፣ ይማልድልናል (ሉቃስ 23፥32)። በእርሱ በጌታ ሙሉነት ስላለ፣ ከሙላቱ ጸጋና ኃይሉን ለእኛ ያስተላልፍልናል።

እየሱስ ክርስቶስ ሁሉ በሁሉ መሆኑን እውቀንና ተረድተን አባት ልጁን እንደሚጠይቅ የሚያስፈልገንን በጎ ስጦታዎች ሁሉ እንጠይቀው፣ እርሱም ይሞላልናል (ማቴዎስ 7፥7፤ 1 ቆሮንቶስ 2፥2)።

ኢየሱስ ክርስቶስን በሙላት ሳናውቅ፣ ራሳችንንም በሚገባ አናውቅም። ያለ ጌታም እኛ በራሳችን አንዳች ማድረግ አንችልም (ዮሐንስ 15፥5)።

በክርስቶስ ጸጋና ኃይል ስንበረታ፣ የጠላት ሰይጣንን ፈተና፣ የዓለምን መከራና የሥጋን ድካም በድል እንወጣለን (ኤፌሶን 6፥10)።

ንጉሥ ዳዊት ጌታ ከእርሱ ጋር ሰለ ነበር እስራኤላውያን ሊያሸንፉት ያልቻሉትን ክፉ የፍልስጥኤም አለቃ ጎልያድን ማሸነፍ እንደ ቻለ፣ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ካለ፣ የዓለምን ፈተናና የሰይጣንን ወጥመድ እናሸንፋለን (1 ሳሙኤል 17፤ ሮሜ 8፥37)።

የትንሣኤ ሕይወትና ኃይል

በሳሙኤል ብሬንግል (Samuel Brengle)

“ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተሰፋና ለማይጠፋ እድፈትም ለሌለበት ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ” (1 ጴጥሮስ 1፥3)።

የጌታ ትንሣኤ አምላክነቱን የሚያረጋግጥና ለተከታዮቹ ሕይወትና ኃይል የሚሰጥ ብርቱ መልእክት ነው። “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ . . . እርሱን ስሙት” ብሎ እግዚአብሔር የተናገረለት ጌታችን ኢየሱስ

ክርስቶስ ሁሉም ወደ እርሱ ሊመጣ እንደሚገባ መጥምቁ ዮሐንስ የተናገለት ሞትን አሸንፎ የተነሣውና በክብር የሚመለሰው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴዎስ 3፥17)።

ይህ ከሞት የተነሣው ክርስቶስ የብርታት፣ የኃይል፣ የጭምትነትና ራስን የመግዛት ዘላለማዊ መንፈስ እንደሚሰጠን ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ አረጋግጦልናል (ሮሜ 1፥4)።

ማዕበሉ፣ ወጀቡ፣ የኑሮው መከራና እንግልቱ ሲደራረብብን ደቀ መዛሙርቱ እንደ ጠሩት እኛም ብንጠራው፣ የከበበንን ወጀብና ዓውሎ ንፋስ ጌታ ያሰወግድልናል። ለዚህም እምነት እንዲኖረን ያሳሰበንን ተከትለን በእምነት እንድንሞላ በቃሉና በጸሎት ልንተጋ ያሰፈልገናል (ማርቆስ 4፥38)። በዘመናችን የሚያጋጥሙንን ችግሮችና ፈተናዎች ልንመክት የሚያስችለን የጌታ ዘላለማዊ ቃልና ቅዱስ መንፈሱ ናቸው (ዮሐንስ 16፥29፤ ኤፌሶን 3፥16)።

በሰውና በመላእክት፣ በነቢያትና በሐዋርያት ሰብአዊ አስተሳሰብ የዓለምን ኃጢአትና በደል ለማሰወገድ በቀራንዮ መስቀል ላይ የተሰቀለውን ጌታ እንደሚገባው ሊቀበሉት አልቻሉም። ለብዘዎች ዛሬም ድረስ የመስቀሉ ቃልና ድርጊት ሞኝነት ሲሆን፣ ለእኛ ለምንድነው የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ነው (1 ቆሮንቶስ 1፥1-18፣1 ቆሮንቶስ 1:25)።

የክርስቶስ ትንሣኤና የእኛ አዲስ ሕይወት

(በቻርለስ ስፐርጂን/Charles H. Spurgeon)

“እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን” (ሮሜ 6፥4)።

አማኞች በክርስቶስ ጥበብን ሁሉ ይቀዳጃሉ። ጸጋና ፍቅሩ ከኃይሉ ጋር ይሰጣቸዋል። ክርስቶስ ሞቶ እንዳልቀረ ሁሉ፣ በትንሣኤው ያሳየው ኃይል ለአማኞችም የሕይወት ለውጥ የአዲስ ሕይወት ልምምድ ሰጭ ነው።

ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት አምነው ሲመላለሱ፣ አዲስ የሕይወት ልምምድ በሕይወታቸው ይታያል። የድሮ ወዳጆቻቸው

ዘመዶቻቸው እስከሚደነቁ ድረስ ያ አዲስ ሕይወት የተገለጠና የሚታይ ይሆናል (ማቴዎስ 5፥16፤ 1 ዮሐንስ 5፥11፤ ኤፌሶን 5፥8)።

“እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁ የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ናችሁ” (1 ጴጥሮስ 2፥9)። በክርስቶስ የሚገኘው አዲስ ሕይወት ተስፋ ያለበት ነው። ሰዎች ለጉዳት ለሞት ለበሽታ ብዙ ጊዜ የሚዳረጉት የሕይወት ተስፋ ሲያጡ ነው። በክርስትና ግን እውነተኛ የሕይወት ተስፋ ስለ ተሰጠን፣ ክርስቲያኖች በዚህ ተስፋ እንኖራለን (ኢሳይያስ 55፥12፤ ማቴዎስ 6፥32)።

ለውጥ የእግዚአብሔርና የተፈጥሮ ሂደት ነው። በጎ ለውጥ እንዳለ ሁሉ፣ ክፉ ለውጥም ይገኛል። ክርስቲያኖች የምናምነውና የምንለማመደው ለውጥ ግን በጎ የሆነውን፣ ሰዎችን ለመንፈስም ለሥጋም ወደ በጎነትና ወደ መልካምነት የሚያሻግረውን ለውጥ ነው (ዮሐንስ 3፥17፣ ምሳሌ 3፥5)። ይኸውም ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከክፋት ወደ ደግነት፣ ከርኩሰት ወደ ቅድስና ናቸው።

የእማኞች እይታ ከፍ ያለና ሰማያዊ ነው

(በቻርለስ ሰፐርጂን/Charles H. Spurgeon

“እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁ በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፤ ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ” (ቆላስይስ 3፥1-4)።

በምድራችንና በመላው ዓለም ጦርነቶች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ፤ ተዋጊዎች ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ፣ ልዩ ልዩ ስልቶችን ያካሂዳሉ፤ ውጊያዎቹ መንፈሳዊና ሥጋዊ ናቸው።

የውጊያው ስልፍ መሪዎችና ተከታዮች በእንድ በኩል ክርስቶስና የእውነት፣ የፍትሕ፣ የቅድስና ሠራዊት፣ በሌላው በኩል የሰይጣንና የርኩሰት፣ የግፍ፣ የጭቆና ሠራዊት ናቸው።

እጅግ የሚያሳዝነው፣ የአስላለፍ ስሕተትና ማጭበርበር የሚካሄደው ሰዎች የግፍ የኃጢአት ሥራዎችን፣ በደሎችን ጭቆናዎችን በሌሎች ላይ እየፈጸሙ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ሠራዊት ማድረጋቸው ነው። ይህን እታላይ አስላለፍ የዋህ አማኞችንና የክፉ ገዢዎችና ዘረኞች እንደ ትክክለኛ ሠራዊት በማድረግ ማቅረባቸው ሲሆን፣ እውነተኛ የጌታ ልጆች ግን በቅዱስ ቃሉና በመንፈሱ እውነተኞቹ ከሐሰተኞቹ የመለየት ሥልጣንና ብቃት ተሰጥቷቸዋል።

ለውጊያዎቹ ትክክለኛ አስላለፍና ምርኮ የሚረዳውና የሚያበቃን የሚደረጉትን ውጊያዎች በሰማያዊ እይታ በመቃኘቱና ከመዋጋቱ እንጻር ይሆናል (ኤፌሶን 6፥12)። ክፉ ሰይጣን በቅዱስ ቃሉ በሰማያዊ ትጥቅ የተሞሉትን እንደ መሪ አዝማቻቸው ክርስቶስ ሊቋቋም አይችልም። በቅዱስ ቃሉ መሣሪያ ይደቅቃሉ። ቅዱስ ቃሉን እንታጠቅ (ኤፌሶን 6፥13)

ድሉ የጌታችን ነው እኛም በክርስቶስ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

ልብን የሚፈትኑ የወቅቱ ጉዳዮችና መጠይቆች

(በዳን ማክላንታየር/Don Maclntyr)

መንፈሳዊ መነቃቃት የተጠሙ ሁሉ ሊያተኩሩባቸው የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፦

1. ራሳችሁን የጠፋችሁ አድርጋችሁ በማየት ልባችሁ ለኃጢአት ምክንያት እንደሚሆን ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? (ትንቢተ ኢሳይያስ 6፥5)

2. ጌታን አምናችሁ የምትጓዘት በምን መሰፈርት ነው? በተለወጠ ሕይወት፣ በኃጢአት በመናዘዝና በክርስቶስ በመታመን ነውን? (ማቴዎስ 4፥17)

3. ከኃጢአታችሁ ለመገላገል ያላችሁ ፍላጎት ምን ያህል ነው? ከዓለም ፍላጎትና ከሥጋ ሥራ ለመለየት ምን ያህል ጥረት ታደርጋላችሁ? (ገላትያ 5፥24)

4. ኢየሱስ ክርስቶስን እምኖ በመከተል የሚያስከትለውን መገፋት፣ መሰደድ፣ መጎዳትና መገለል ለመቀበል የተዘጋጃችሁ ናችሁ? (ማርቆስ 8፥34)

5. ሕይወታችሁን በሙሉ ለጌታ በመሰጠት ከዓለምና ከሥጋ ለመለየት ወሰናችኋልን? (ዮሐንስ 6፥66) በመከራ ብዛት ወደ ኋላ አትመለሱምን?

6. በጌታ ኃይላችሁ እንደሚታደስ እስከ መጨረሻ እንደምትጸኑና ጌታን እንደምትጠባበቁ ለራሳችሁ ቃል ገብታችኋልን? (ኢሳይያስ 40፥31)

7. በሁሉም ሁኔታ ለመጸለይ ፍላጎት አላችሁን? በየምክንያቱ ከጸሎት ኅብረት ላለመቅረት ለራሳችሁ ቃል ገብታችኋል? (1 ተሰሎንቄ 5፥17)

8. በየዕለቱ የእግዚአብሔር ቃል ረሀብ አላችሁን? ለሥጋችሁ ምግብ እንደምትሹት፣ ለነፍሳችሁ ቅዱስ ቃሉን ትናፍቃላችሁን? (1 ጴጥሮስ 2፥2፤ መዝሙረ ዳዊት 119)

9. በሁሉም ጊዜና ሰፍራ ጌታን ለማክበር የተዘጋጃችሁ ናችሁ? (መዝሙረ ዳዊት 34፥1፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥)።

10. በሕይወታችሁ በምትኖሩበትና በምትሠሩበትና በምትማሩበት ሰፍራ ከክርስቶስ ታቦር ላይ (ማቴዎስ 5፥16) በመልሶቻችሁ ተሰፋ ሳትቆርጡ የጎደላባችሁን በማሟላት ለክርስቶስ ታበራላችሁን?

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእሶችና ምስክርነቶች

ሕንድ

እጅግ ለምባረክበት ለየምጽአቱ የምሰራች ጋዜጣ አድናቆቴን የምገልጥበት በቂ ቃል የለኝም። በዓለም በሕዝብ ብዛት ቀዳሚ በሆነችውና ልዩ ልዩ ክፉ መናፍስት የሚሠለጥኑባት ክርስቲያኖችን በማሳደድ በስሜን ኮሪያ ከሚመሩት 12 ሀገሮች ውስጥ 12ኛ ለሆነችው ሕንድ በብርቱ ጸልዩ።

ከናይጄሪያ

በየጊዛው ለምትልኩልን የምጽአቱ የምሰራች መንፈሳዊ ምግብ ከልብ እናመሰግናለን። ለብዙ አገልጋዮች ትልቅ ድጋፍ የሚሰጠውን ጋዜጣችሁን ከመላክ አታቋርጡብን። ከአፍሪካ በሕዝብ ብዛት አንደኛ ለሆነችው ናይጄሪያ ጸሎት አድርጉልን። ብዘዎች በጨለማ ያሉትን በፍቅር እንድንመልሰ የይቅርታና የምሕረት ልጆች እንድንሆን ጸልዩልን።

ከእንግሊዝ

ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ዳግም ተወልጄ የጌታን ሥራ በቃሉ ጥናት አገለግላለሁ። የቀደመችው የወንጌላውያን መልእክተኞች ላኪ እንግሊዝ እንድትፈወስና ወደ ጌታ ክብር እንድትመለስ ጸልዩልን።

ለእሰራኤል እንጸልይ

የክርስቲያኖች ምሳሌ ሆና በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ቃሉን ያስተላለፈባት መሲሑን ዛሬ ድረስ ከ2 በመቶ ያነሱ መሲሐውያን ብቻ ለሚያምኑባት እሰራኤል እንጸልይ (መዝሙረ ዳዊት 122፥6)።

ለምርጫ ጸሎት ይደረግ

በልዩ ልዩ ሀገሮች ለፖለቲካና የምርጫ ውድድር፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ ጌታ የታመኑ መሪዎችን እንዲያሰቀምጥ በብርቱ እንጸልይ።

ለአብያተ ክርስቲያናት ለሕብረቱ እንጸልይ

በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካ ላሉ የወንጌላውያን ሕብረት መሪዎች እንጸልይ።

የሁለቱም መሪዎች የአማኑኤል ሕብረት የምጽአቱ የምሥራችን ከ30 ዓመታት በፊት በፋይናንስ የረዳ የቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸው። ብዘዎቹ የወጡበት ጥንታዊ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ጌታ እንዲባርክ እንጸልይ፣ ብድራቷንም እናሰብ።

ለሚወረሩ፣ ለሚፈናቀሉና ለሚባረሩ እንጸልይ

መጻተኞች በብዙ ተሰፋ ወደ ተሻሉ ሀገሮች ብዙ ገንዘብ ከፍለው ሄደው ለሚባረሩና በገዛ ሀገራቸው ለሚፈናቀሉና ለሚወረሩ እንጸልይ፣ በሚቻለን እንደግፋቸው (ኢሳይያስ 61፥1)።

የምጽአቱ የምሰራች ማሰታወቂያዎችና ምስክርነት

<u>አረብኛው የምጽአቱ የምሰራች ቀጠለ</u>

የአረብኛው የምጽአቱ የምሥራች አሰተባባሪ ተርጓሚ ወንድማችን ፓስተር ሣሚር ጻድቅ ካረፈ በኋላ ተቋርጦ የነበረው አገልግሎት የልጅ ልጁ ባስኔት ሃና ኃላፊነቱን ተቀብላ ሰለ ቀጠለ፣ ጌታን እጅግ እናመሰግናለን። በአረብኛ ለሚፈልጉም በደብዳቤ ጠይቁና አሰራጩ።

<u>የምጽአቱ የምሥራች እርዳታ ይፈልጋል</u>

የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት በበጎ ፈቃድ ለጋሾች መዋጮ ብቻ የሚካሄድ አገልግሎት ነው።

ለዚህ አገልግሎት በጸሎትና በሚቻላችሁ ሁሉ ገንዘብ በፖስታ ቤት በኩል በመላክ ለብዙዎች መድረስ እንድንችልና በገንዘብ እጥረት ማሠራጨት እንዳናቆም ድጋፍ አድርጉልን።

የምጽአቱ የምሥራች አገልግሎት
የፖ.ሣ.ቁ/P.O.Box 8986
Amharic Herald of His Coming
አዲስ አበባ፣ Addis Ababa, Ethiopia.
ሰልክ 0993154034
<u>በኢትዮጵያ ተጠሪ</u>፡- ብርሃኑ ጥርሣማ

<u>የመዳን ምክሮች</u>

1. ኃጢአተኛ ሰለ መሆናችን ቃሉ ሲነካን፣ ንስሐ እንግባና ጌታን ምሕረቱን እንጠይቀው (ሮሜ 3፥23፣ 6፥23)።
2. የእግዚአብሔርን ይቅርታ በቃሉ ተቀብለን ከክፉ መንገዳችን እንመለስ (ትንቢተ ኢሳይያስ 55፥7)።
3. በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ካመንን በኋላ፣ ወዲያውኑ በቅርባችን ወደሚገኝ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሰም ከሚያጠምቁና ከሚያስተምሩ ጋር ኅብረት እንጀምር (ማቴዎስ 28፥19-20)።

Amharic Herald of His Coming
የምጽአቱ የምሰራች አገልግሎት

<u>የአማርኛው አሰተባባሪ</u>፡- ቄስ ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
<u>በኢትዮጵያ ተጠሪ</u>፡- ብርሃኑ ጥርሣማ
<u>አርታኢ</u>፡- ዘነበ ገብረሐና
<u>ታይፕና ዲዚይን</u>፡- አቤኔዘር የጽሕፈት ሥራ፣ መካኒሳ
በሳሚ አሳታሚ ታተመ።
የፖ.ሣ.ቁጥር. /P.O.Box 8986 አዲስ አበባ፣ Addis Ababa, Ethiopia.

በነጻ የሚሰጥ